| | |
|---|---|
| ዐይነት ፲ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፲ | "የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ። " |
| ደራሲ ፲ | ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽ. ፡ ቤት ። |
| ዕለት ፲ | ኅዳር ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፲ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፲ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-002 |
| ማስታወሻ ፲ | |
| ማኅሰቢያ ፲ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | إِفْتِتاحي

## የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ።

---

ከስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በመዠመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ በአጋቦስ ፡ ዘመን ፡ በተካኼደ ፡ ሀገራዊ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መሠረት ፡ የተቋቋመው ፡ ጥንታዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፥ በረዥም ፡ ታሪኩ ፥ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ሀገራዊ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ የተሻሩበት ፡ የጥፋት ፡ ወቅቶች ፡ ቢገጥሙትም ፡ (ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፥ በዮዲት ፡ ጉዲት ፡ የጥፋት ፡ ዘመን ፣ በዛጔ ፡ ዐምባ ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፣ በግራኝ ፡ አሕመድ ፡ ወረራ ፣ በፋሺስት ፡ ኢጣልያ ፡ ወረራ) ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዅል ፡ ጊዜም ፡ ሀገራዊ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ዳግመኛ ፡ እያደሰና ፡ እግዚእናውን ፡ እያስከበረ ፡ መንግሥቱን ፡ መልሶ ፡ በማቋቋም ፡ የሐራነት ፡ ታሪኩን ፡ አስቀጥሏል ።

የዘመናችን ፡ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ የ"አፓትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ በጕልበት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በግፍ ፡ ሲጭኑባት ፥ ተመልሳ ፡ እንዳታንሰራራ ፡ ኾና ፡ የምትፈራርስበትንም ፡ ዐቅድ ፡ ዐብረው ፡ ነድፈውላት ፡ ነበር ። አኹን ፡ ግን ፥ ከኢትዮጵያ ፡ ይልቅ ፥ ራሳቸው ፡ ያነጹትና ፡ በብዙ ፡ ቢልየን ፡ ዶላር ፡ ያደራጁት ፡ የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ቀድሞ ፡ ሊደረመስባቸው ፡ ተቃርቦ ፥ በጥግንግን ፡ ዕድሜውን ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ አራዝመው ፥ ከመሰናበቱም ፡ በፊት ፡ የተፈጠረለትን ፡ የጥፋት ፡ ግብሩን ፡ እንዲፈጽም ፡ ተጠበውለታል ።

ዐምባ ፡ ገነንነት ፥ ለባዕድ ፡ ጥቅም ፡ የተሠራ ፣ የማይጸድቅ ፣ የማያፈራ ፣ ጊዜያዊና ፡ ፈራሽ ፡ ኀይል ፡ ነው ። የኢ..ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘትና ፡ ባዕድ ፡ ሠራሽ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥቱ" ፡ ዕጣ ፡ ፈንታቸው ፡ እንደማይጠገኑ ፡ ኾኖ ፡ መፈራረስ ፡ ነው ። በዕሥሥት ፡ ፖለቲካ ፡ ዅሉን ፡ መስሎ ፡ የሚሠራ ፡ ተንኰል ፡ ዅሉ ፡ ግብዝነቱ ፡ እያደር ፡ ለሕዝብ ፡ ፍንትው ፡ ብሎ ፡ የሚታይ ፡ ስለሚኾን ፥ ከመጠላት ፡ በቀር ፡ ለ"ፖለቲከኞቹ" ፡ የሚያተርፍላቸው ፡ ነገር ፡ አይኖርም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ኹኔታውን ፡ ቀድሞ ፡ የተገነዘበውን ፡ ያኽል ፥ በገቢር ፡ ከአጥፊዎቹ ፡ ቀድሞ ፡ መገኘት ፡ አለበትና ፥ በመላ ፡ ሀገሩ ፥ እግዚእናውን ፣ ባለሀገርነቱን ፡ በማስከበር ፡ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመከወን ፡ መነሣት ፣ መዘጋጀትና ፡ ማድረግ ፡ ይጠበቅበታል ።

በዚህ ፡ ረገድ ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉን ፡ በኅብረቱ ፡ ሲያሟላ ፥ ባሠራር ፡ ረገድ ፥ ከዐፄ ፡ ሥር ፡ አንሥቶ ፡ እስከዘመናውያን ፡ ድንጋጌዎችና ፡ ሥርዐቶች ፥ ከሕዝብ ፡ ቈጠራ ፡ አንሥቶ ፡ እስከክፍላተ ፡ ሀገር ፡ አወቃቀር ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ዐበይት ፡ ጕዳዮች ፡ ዅሉ ፡ በዝርዝር ፡ ተገንዝቦ ፡ መታገል ፡ የመዳኛው ፡ አንዱ ፡ ዋስትና ፡ ይኾናል ። ከዚህ ፡ ጋራ ፥ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ምሥረታን ፡ በተመለከተ ፥ የሀገርንና ፡ የሕዝብን ፡ ሰላምና ፡ አንድነት ፣ ነጻነትና ፡ ደኅንነት ፡ በሚያረጋግጥ ፡ ጥንቁቅ ፡ ስልትና ፡ ወግ ፡ ይከናወን ፡ ዘንድ ፥ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሊመክርበት ፡ ሊጠበብበትና ፡ ሊወስንበት ፡ ይገባል ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።